# የኤሌክትሮኒክስ የጭነት መቆጣጠሪያ መሣሪያዎችን ወጪና ገቢ ዕቃዎች በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች ስለመጠቀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 134/2013

በወጪና ገቢ ዕቃዎች ማጓጓዝ ሂደት የሚፈፀሙ ወንጀሎች ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሱና አፈፃማቸውም እየረቀቀ በመምጣቱ፤

እነዚህን ወንጀሎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀፅ 20/2/፣ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 112/2/ እና አንቀፅ 107 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኤሌክትሮኒክስ የጭነት ደህንነት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን ወጪና ገቢ ዕቃዎች በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች ስለመጠቀም የወጣ መመሪያ ቁጥር **134/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፤

1) **"መሳሪያ"** ማለት በተሽከርካሪው ወይም በጭነቱ ወይም በኮንቴነር ላይ በማሽጊያ ወይም በመቆለፊያ መልክ የሚገጠም ሲሆን የተሽከርካሪውን የጉዞ መስመርና የተጫነውን ጭነት እንደዚሁም የራሱን (የመሳሪያውን) ደህንነት የሚቆጣጠርና ለመቆጣጠሪያ ማዕከላት ወዲያውኑ (Real time) ወይም በመቆጣጠሪያ ጣቢያ ለሚደረግ (Relevant time) ቁጥጥር የዳታ መረጃ የሚሰጥ ኤሌክትሮኒክስ የጭነት መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ በዚህ መመሪያ "ኤሌክትሮኒክስ ጭነት መቆጣጠሪያ መሳሪያ" የሚለው ሀረግ /ኤ.ጭ.መ.መ./ በሚል አህፅሮተ ቃል በተለዋጭ ይገለፃል፡፡

2) **“የጭነት ወይም መሳሪያ ደህንነት”** ማለት በተሽከርካሪው የተጫነው ዕቃ (ጭነት) አጠቃላይ ይዘት በተጫነበት ጊዜ በነበረበት ሁኔታ ያለ ወይም ያልተፈታ፣ ያልተከፈተ፣ ያልተቀነሰ ወይም የማሸጊያ የመቆለፊያ መሳሪያዎቹ ያልተከፈቱ፣ያልተገነጠሉ ወይም የዚሁ ዓይነት ሙከራ ያልተደረገባቸው መሆኑን፤ ወይም የነዚህ ሁኔታዎች ተቃራኒ ስለመፈፀሙ የሚገለፅበት ነው፡፡

3) **“ዳታ”** ማለት የአንድን ጭነት መነሻ፣ መድረሻ፣ ዓይነት፣ መጠን፣ ሳኪ፣ ተቀባይ የመሳሰሉት መረጃዎች የሚገለፅበት እና ከመሳሪያ የሚገኝ ወይም ከመሳሪያው ጋር ተያያዥነት ካላቸው ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚገኝ፤ ወይም ወደነዚህ መሳሪያዎች እንዲገባ የሚደረግ መረጃ ነው፡፡

4) **“ዳታ መጫኛ መሳሪያ”** ማለት መሳሪያ ውስጥ የዳታ ግብዓት እንዲኖር የማድረጊያ ቴክኖሎጂ ነው፡፡

5) **“ዳታ ማንበቢያ መሳሪያ”** ማለት በመሳሪያ ውስጥ የሚገኘውን ዳታ መቀበልና መረዳት የሚያስችል ቴክኖሎጂ ነው፡፡

6) **“ኤሌክትሮኒክስ የጭነት ደህንነት መቆጣጠሪያ ሥርዓት”** ማለት ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን በመጠቀም የጭነት ደህንነትን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ማለት ነው፡፡

7) **“ኤሌክትሮኒክስ ማሸጊያ”** (Electronics Seal) ለተጫነው ዕቃ ፣ የአስመጪ፣ ሳኪ፣ ኢንቮይስ፣ የማስጫኛ ሰነድ የመሳሰሉት ዝርዝር መረጃ የያዘ በኮንቴነር ላይ ወይም በክፍት ዕቃ መጫኛ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚገጠም መረጃ የሚያስተላልፍና ደህንነትን የሚያስጠብቅ መሳሪያ ነው፡፡

8) **“ዋና መቆጣጠሪያ ማዕከል”** ማለት በባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት የሚገኝና በዋናው መ/ቤት ሥር ሆኖ በጭነት ማጓጓዣና በመሳሪያ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር የሚከታተል የህግ ማስከበር የሥራ ክፍል ነው፡፡

9) **“መቆጣጠሪያ ጣቢያ”** ማለት የጭነት፣ የማጓጓዣውንና የመሳሪያውን ደህንነት ሁኔታ የሚቆጣጠር፣ ከመነሻ እስከ መድረሻ ጣቢያ (በጉዞ መስመር) ባለው መስመር ላይ የሚገኝና መነሻንና መድረሻ ጣቢያን የሚያካትት የጉምሩክ የቁጥጥር ኬላ ነው፡፡

10) **“የቅፅበታዊ ጭነት ቁጥጥር ሥርዓት** (Real time monitoring system)” ማለት የጭነቱን፣ የማጓጓዣውንና የመሳሪያውን ደህንነት በተመለከተ ክትትል በማድረግ መረጃው ወዲያውኑ የሚተላለፍበት ሥርዓት ነው፡፡

11) **"የኬሳ ሳይ መቆጣጠሪያ ሥርዓት** (Relevant time monitoring System)" ማለት ተሽከርካሪው በመቆጣጠሪያው ጣቢያ ሲደርስ የጭነቱን፣ የማጓጓዣውንና የመሳሪያውን ደህንነት በተመለከተ የተሰበሰበው መረጃ የሚተሳሰፍበት ሥርዓት ነው፡፡

12) **"የመጠቀም ግዴታ"** ማለት ማንኛውንም ወደ አገር የሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣን ዕቃ የሚያጓጉዝ ተጠቃሚ ወይም ዕቃ አጓጓዥ በሚያጓጉዝበት ጊዜ በማጓጓዣው ወይም በጭነት ሳይ የሚገጠም መሳሪያ፣ ወይም መሳሪያዎችን የመገልገልና በሥራ ሳይ ማዋል ያለበት መሆኑን ወይም ማንኛውም አጓጓዥ ተሳሳፊ ዕቃዎችን በሚያጓጉዝበት ጊዜ መሳሪያዎችን በሥራ ሳይ እንዲያውል በተጠቃሚ ሳይ የተጣለ ግዴታ ነው፡፡

13) **"ተጠቃሚ"** ማለት ማንኛውንም የወጪና ገቢ ዕቃዎችን የሚያጓጉዝ ተሽከርካሪ ባለቤት ወይም የጋራ ባለቤቶችን የሚጨምር ሆኖ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው ነው፡፡

14) **"የተጠቃሚው ሠራተኞች"** ማለት የተጠቃሚውን ማጓጓዣ የሚያሽከረክር፣ ረዳቱ፣ ወይም የተጠቃሚው ወኪል ወይም የማጓጓዣ ኃላፊው ናቸው፡፡

15) **"አቅራቢ"** ማለት ብቃት ያላቸው መሳሪያዎችን ከባለሥልጣኑ በሚሰጥ ዕውቅና መሠረት ለሽያጭ የሚያቀርብና አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

16) **"ብቃት ያለው መሳሪያ"** ማለት በአገልግሎት ዘመኑ፣ በጥራቱ፣ በመለዋወጫና ተጓዳኝ ዕቃዎቹ አቅርቦት ወይም ቦርዱ የሚወስናቸው ሌሎች መስፈርቶችን የሚያሟሳ መሳሪያ ነው፡፡

17) **"አገልግሎት ሰጪ"** ማለት አቅራቢ ወይም በአቅራቢ ኃላፊነት ለመሳሪያው የተሟሳ አገልግሎት መስጠት የሚችል የአገልግሎት መስጫ ተቋም ያለው ሰው ነው፡፡

18) **"አገልግሎት መስጠት"** ማለት ተጠቃሚው ለገዛቸው መሳሪያዎች ብቃት ያለውና አስተማማኝ የጥገና፣ የእደሳ፣ የመለዋወጫ፣ የወቅታዊ እደሳ የተሟሳ አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡

19) **"አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች"** ማለት በአገልግሎት መስጠት ሂደት ተሳትፎ ያላቸው የአገልግሎት ማዕከሉ ባለሙያዎች፣ ኤክስፐርቶች፣ ማኔጀሮች ወይም ለእነዚህ ድጋፍ የሚሰጡና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

20) **"የአገልግሎት መስጫ ተቋም"** ማለት በአቅራቢው ሰው የሚቋቋምና የሚተዳደር ወይም ከአቅራቢው ጋር በሚደረግ ስምምነት በሌሳ ሰው የሚቋቋም አገልግሎት መስጠት የሚያስችል አቋምና በቂ የአገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች ያሉት ድርጅት ነው፡፡

21) **"ኤሌክትሮኒክስ መረጃ"** ማለት ከመሳሪያዎች የሚገኝ ወይም ከኤሌክትሮኒክስ ሥርዓቱ የሚገኝ የተጠናቀረ ዳታ ወይም የዳታ ስብስብ ነው፡፡

22) **"የኤሌክትሮኒክስ መረጃ አግባብነት"** ማለት የኤሌክትሮኒክስ መረጃ በመሳሪያ ሳይ ወይም በማጓጓዣ ጭነት ላይ ስተፈፀመ ተግባር እንደማስረጃ በሕግ ያለው ተቀባይነትን የሚመለከት ነው፡፡

23) **"ቦርድ"** ማለት ስመሳሪያ አቅራቢዎች፣ ስመሣሪያዎች የሚቀርበዉን የዕውቅና ወይም ዕውቅናን የመሠረዝ ጥያቄ የሚመረምርና እውቅናና ፈቃድ እንዲሰጥ ወይም እንዲሰረዝ ስባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰየም አካል ነው፡፡

24) **"ወቅታዊ አገልግሎት"** ማለት ስመሳሪያዎች እንደአስፈሳጊነቱ በመደበኛነት በየሩብ ዓመት የጊዜ ልዩነት የሚሰጥ አገልግሎት ነው፡፡

25) **"ባለሥልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

26) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት ያገኘ ማንኛውም ህጋዊ ተግባራትን መፈፀም የሚችል አካል ነው፡፡

27) **"አዋጅ"** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የገቢና የወጪ ዕቃዎች ጭነት በማጓጓዝ ሥራ ላይ በሚሰማራ የንግድ ተሽከርካሪ፣ ከዚሁ ጋር ግንኙነት ባላቸው አካላት (ተጠቃሚ፣ አቅራቢ፣ የአገልግሎት ሰጪ) እና ሌሎች በተመሳሳይ ተግባራት ላይ በሚሰማሩ ወይም እነዚህኑ በሚቆጣጠሩ ሰዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የተጠቃሚ እና የሠራተኞቹ ግዴታ

## 4. የተጠቃሚ ግዴታ

### 1) የማሸጊያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ

ሀ/ ማንኛውም ተጠቃሚ ተሽከርካሪውን ስወጪና ገቢ ዕቃዎች ማጓጓዝ ተግባር በሚያውልበት ወቅት መሳሪያውን የመጠቀም ግዴታ አለበት፡፡

ለ/ ለአንድ ተሽከርካሪ ከአንድ በላይ የማሽጊያ መሳሪያዎች መጠቀም የሚያስፈልገው ሲሆን ተጠቃሚው ይህንኑ የማሟላትና የመጠቀም ግዴታ አለበት፡፡

ሐ/ ባለሥልጣኑ እንደአስፈላጊነቱ ለመሳሪያው መለያ የመስጠት፣ ለአንድ ተሽከርካሪ የሚያስፈልገውን ከአንድ በላይ መሳሪያ የመጠቀም ሁኔታን ይወስናል፡፡

2) <u>የመሳሪያ ግዥ እና ማሳወቅ</u>

ሀ/ ተጠቃሚ የማሽጊያ መሳሪያውን ባለሥልጣኑ እውቅና ከሰጠው አቅራቢ ብቻ መግዛት አለበት፡፡ መሳሪያው በአቅራቢው መመዝገቡን እና አስፈላጊ ሰነዶች የተሟሉለት መሆኑን ማረጋገጥና መያዝ የተጠቃሚው ግዴታ ነው፡፡

ለ/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /ሀ/ የተጠቀሰው ቢኖርም ተጠቃሚው በዚህ መመሪያ የሚጠየቀውን መስፈርት የሚያሟላ መሳሪያ በራሱ በማቅረብ እንዲጠቀም ባለስልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ተጠቃሚው በራሱ አቅራቢነት ለሚጠቀመው መሳሪያ በዚህ መመሪያ የተገለፁጽ የአቅራቢነት ግዴታዎች ተፈፃሚ ይሆኑበታል፡፡

3) <u>የማሽጊያ መሳሪያውን ደህንነትና አጠቃቀም የመከታተል ግዴታ</u>

ሀ/ ተጠቃሚው መሳሪያው በተገቢው ሁኔታ የተያዘ፣ ለሥራ ብቃት ያለው፣ ጉዳት ያልደረሰበት፣ እና ወቅታዊ አገልግሎት የተደረገለት መሆኑን መቆጣጠር አለበት፡፡

ለ/ ተጠቃሚው መሳሪያውን በሥራ ላይ ከማዋሉ በፊት ስለመሳሪያው አጠቃቀም፣ አገልግሎት አሰጣጥ፣ አገጣጠም እና አስተሻሸግን በተመለከተ ሠራተኞቹ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ አለበት፡፡

ሐ/ ተጠቃሚው የገቢና ወጪ ጭነትን ማጓጓዝ ከመጀመሩ በፊት በመነሻ ቦታ፣ በመተላለፊያ መስመር ማጓጓዝ ሂደት እና በመድረሻ ጣቢያ መሳሪያውን በመጠቀም ረገድ ተገቢው ሥርዓት መፈፀሙን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡

4) <u>ሠራተኞችን የመቆጣጠር ኃላፊነት</u>

ሀ/ ተጠቃሚው በሥራ ላይ የሚያሰማራቸው ሠራተኞች በህግ የተመለከቱትን ኃላፊነቶች በተገቢው መገንዘብ የሚችሉ ይህንንም በታማኝነት የሚፈፅሙ ስለመሆናቸው የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

ለ/ ተጠቃሚው ሠራተኞቹ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያን በመጠቀም ረገድ ይህንን መመሪያ በመተላለፍ የሚጣልባቸውን የገንዘብ መቀጫ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

## 5) መሳሪያን ስለማስተላለፍ

ሀ/ ተጠቃሚው ለተወሰነው ማጓጓዣ ብቻ እንዲጠቀምበት የተፈቀደለትን መሳሪያ ያለባለስልጣኑ ፈቃድ ለሌላ ተሽከርካሪ መጠቀም አይችልም፡፡

ለ/ ተጠቃሚው ለራሱ ማጓጓዣ የተፈቀደለትን መሳሪያ ያለባለሥልጣኑ ፈቃድ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይችልም፡፡

ሐ/ ተጠቃሚው መሳሪያውን በእርጅና፣ በብልሽት ወይም የማጓጓዝ ሥራውን በመተው ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ ለማድረግ ወይም ለማስወገድ በቅድሚያ ባለሥልጣኑን ማሳወቅና ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

## 6) የተጠቃሚ ሠራተኞች ግዴታ

### 1) ስለ መሳሪያዎች ደህንነት

ሀ/ የመጓጓዣ ኃላፊው በማጓጓዝ ሥራ ላይ ከመሰማራቱ በፊት መሳሪያዎቹ ለሥራ ብቃት ያላቸው ፣ያልተበላሹ፣ ወቅታዊ አገልግሎት የተደረገላቸው እና ለተጠቀሰው ማጓጓዣ ሥራ ላይ እንዲውሉ የተፈቀዱ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ለ/ የማጓጓዣ ኃላፊው ወይም ረዳቱ በማጓጓዝ ሂደት ወይም በመተላለፊያ መስመር ወይም ማጓጓዣው በሚቆምበት ቦታ በአጠቃላይ ከመነሻ እስከ መድረሻ መሳሪያዎቹ በሥራ ላይ መሆናቸውን ወይም በማንኛውም ሁኔታ ጉዳት ወይም መነካካት እንዳይፈፀምባቸው የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

ሐ/ የመጓጓዣ ኃላፊው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ /ለ/ የተጠቀሰውን በመተላለፍ የተፈፀሙ ማናቸውንም ተግባሮች ወይም ሙከራዎች በመሳሪያው ላይ የደረሰ ጉዳት ቢኖርም ባይኖርም ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ ወይም የጉምሩክ ጣቢያ በቅርብ በሌለበት በአቅራቢያ ለሚገኝ የፌደራል ፖሊስ ወይም ሌሎች የክልል የህግ አስከባሪ አካላት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

መ/ የመጓጓዣ ኃላፊው የሕግ መተላለፉን ለመንግሥት የህግ አስከባሪና አስተዳደር አካላት ቢያሳውቅም በተጨማሪ በቅርበት ለሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

ሠ/ የመጓጓዣ ኃላፊው የሕግ መተላለፍን ያሳወቀው ከመድረሻ የጉምሩክ ጣቢያ ውጪ ሲሆን በተገኘው የመገናኛ ዘዴ ሁሉ በመጠቀም ወይም ይህን ማድረግ ባልቻለበት ጊዜ ለመድረሻ ጣቢያው ዝርዝር ሁኔታውን እንደደረሰ በጽሑፍ ሪፓርት ማድረግ አለበት፡፡

2) **ተገቢውን ሥርዓት የመፈፀም ግዴታ**

ሀ/ የመጓጓዣ ኃላፊ በመነሻ፣ በጉዞ ላይ፣ በመድረሻ፣ በመግቢያ ወይም በመውጫ የጉምሩክ ጣቢያ ወይም ዕቃ በመጓጓዣ ከተጫነበት ቦታና ጊዜ ጀምሮ መሳሪያው ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ እንዲችል የሚያስፈልገው የዳታ መጫን፣ የማሸግ እና የመሳሰሉት ሥርዓቶች በተገቢው መፈፀማቸውን እና ለማጓጓዝ የተፈቀደለት መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

ለ/ የማጓጓዣ ኃላፊው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /2/ /ሀ/ ዓይነት በመተላለፊያ የመቆጣጠሪያ ጣቢያና በመድረሻ ጣቢያ መፈፀማቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

ሐ/ የኤሌክትሮኒክስ ማሸጊያ (Electronic seal) መሳሪያን በጭነት ተሽከርካሪ ላይ የማሸግ፣ ዳታ የመጫን፣ ዳታ የማስተላለፍ ኃላፊነት በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚገኝ የጉምሩክ ሹም ነው፡፡

## 7. <u>ክልከላ</u>

1) ማንኛውም ሰው ያልተፈቀደለትን ወይም ለተወሰነ ማጓጓዣ የተፈቀደን መሳሪያ በማጓጓዣው መጠቀም፣ ወይም ሌሎች እንዲጠቀሙበት ማድረግ ወይም በባለሥልጣኑ ሳይፈቀድለት በይዞታው ሥር ማድረግ አይችልም፡፡
2) በባለሥልጣኑ ከተፈቀደለት በስተቀር ማንኛውም ሰው በማጓጓዣ ላይ የተገጠመን ወይም በሥራ ላይ ያለን መሳሪያ መንካት፣መፍታት እና ወይም የመሳሰሉትን ድርጊቶችን መፈፀም ወይም መሞከር የለበትም፡፡
3) ማንኛውም ተጠቃሚ ወቅታዊ አገልግሎት ያላገኘን መሳሪያ መጠቀም የለበትም፡፡
4) መሳሪያውን ከሸጠው አቅራቢ በስተቀር ማናቸውም ሰው መሳሪያ መጠገን፣ ለውጥ ማድረግ፣ አቅም ማሳደግ ወይም ወቅታዊ አገልግሎት የማድረግ ሥራ ማከናወን አይችልም፡፡

## 8. የመሳሪያ መጥፋትንና ብልሽትን ማሳወቅ

1) ተጠቃሚው ለራሱ ማንንዣ ለመጠቀም የተፈቀደለት መሳሪያ ተገቢዉን ጥበቃና አያያዝ ከማከናወን ግዴታው በተጨማሪ የመሳሪያው ብልሽት ወይም መጥፋት እንደተከሰተ ይህንኑ ለአቅራቢውና ለባለሥልጣኑ ወዲያውኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
2) የማንንዣ ኃላፊው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተገለፀው የብልሽት ወይም የመጥፋት ሁኔታ በማንንዝ ሥራ ላይ ባለበት ሁኔታ ሲያጋጥም በአቅራቢያው ለሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ፣ የጉምሩክ ጣቢያ በሌለበት አካባቢ በአቅራቢያው ለሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ህግ አስከባሪ አካላት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 9. የማስረዳት ኃላፊነት

የመንንዣ ኃላፊ ወይም ረዳቱ በማንንዝ ወይም በሥራ ላይ ባሉበት ጊዜና ሁኔታ በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በመሳሪያ ላይ ጉዳት ቢደርስ፣ ቢነካካ ወይም በጭነቱ ደህንነት ላይ የተከናወነ ህገወጥ ድርጊት ወይም ይህንኑ የማድረግ ሙከራ መኖሩ ሲታወቅ ድርጊቱ በነሱ ያልተፈፀመ ስለመሆኑ የማስረዳት ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

## 10. ለውጥን ማሳወቅ

ተጠቃሚው አስቀድሞ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ሳያሳውቅና ፈቃድ ሳያገኝ በመሳሪያው ላይ የጥገና፣ አቅም የማሳደግ፣ ለውጥ የማድረግ፣ የማሻሻል ወይም ወቅታዊ እደሳ የማድረግ ሥራ ማከናወን የለበትም፡፡

# ክፍል ሦስት

# ስለመሳሪያ እና አቅራቢዎች ዕውቅናና ምዝገባ

## 11. ስለ አቅራቢነት ዕውቅና

ማንኛውም ሰው መሳሪያዎችን ለሽያጭ ለማቅረብ በቅድሚያ የአቅራቢነት እና የመሳሪያ ብቃት ዕውቅና በባለሥልጣኑ በሚቋቋም ቦርድ ሊሰጠው ይገባል፡፡

## 12. የአቅራቢነት ዕውቅና ለማግኘት ለቦርዱ የሚቀርብ ማመልከቻና ተያያዥ ሰነዶች

1) መሳሪያዎቹን ለማቅረብ እና ብቃት ያለው አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአገልግሎት ተቋምና አቅም ያለው መሆኑን የሚያረጋግጡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች ከማመልከቻቸው ጋር አያይዞ ያቀርባል፡፡

   ሀ. ስለሚያቀርባቸው መሳሪያዎችና ስለሚያገኛቸው አገልግሎቶች ከአምራቹ ጋር ቢያንስ ለ5 ዓመት የገባውን የስምምነት ሰነድ፤

   ለ. ከብር ሃያ ሚሊዮን ያላነሰ ካፒታል ያለው መሆኑን የሚያስረዳ ሰነድ፤

   ሐ. ስለመሳሪያው አለም አቀፍ ብቃት ማረጋገጫ በአባሪ I እና II መሠረት በቦርዱ የሚጠይቀውን መስፈርት የሚያሟላ፤

   መ. ብቁ የባለሙያ ስብጥር ያለው መሆኑን የሚገልፁ ሰነዶች ይሆናሉ፡፡

2) አቅራቢው ወይም ሠራተኞቹ፣ አገልግሎት ሰጪዎቹና ተቋሙ ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው በህግ ለሚጣልባቸው መቀጫ የሚውል የ2 ሚሊዮን ብር የመድን ዋስትና የሚያቀርብ፤

3) በንግድ በተሰማራበት ጊዜ የግብር ግዴታውን በአግባቡ ለመወጣቱ የሚያረጋግጥ ሰነድ፤

4) በዚህ አንቀፅ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች የሚያሟላ መሆኑን የሚገልፅ የጽሑፍ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፡፡

## 13. የመሳሪያ አቅራቢ ግዴታ

1) አቅራቢው በባለሥልጣኑ የአቅራቢነት ዕውቅና እንዲያገኝ ያስቻሉትን መስፈርቶች ማክበር አለበት፤

2) አቅራቢው ዕውቅና ሳገኝባቸው መሳሪያዎች ሽያጭ ካከናወነ ጊዜ ጀምሮ ቢያንስ ለ5 /አምስት/ ዓመት በቂ የሆነ መለዋወጫ ማቅረብ አለበት ወይም ለማቅረብ የሚያስችል ዋስትና መስጠት አለበት፡፡

3) አቅራቢው ላቀረባቸው ዕቃዎች ብቃት ያለው የጥገናና የወቅታዊ አገልግሎት /ሰርቪስ/ በተገቢው ጊዜ መስጠት አለበት፡፡

4) የመሳሪያ አቅራቢ በየጊዜው ከውጪ የሚያስመጣቸውን የመሳሪያዎች ዝርዝር በአባሪ V ቅፅ መሠረት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

5) አቅራቢው የሚሸጣቸውን መሳሪያዎች በመግለጫዎች በማስደገፍ ለባለሥልጣኑ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

6) የሽያጭ ወይም አገልግሎት ሰጪ ሠራተኞች በሚፈፅሙት ጥፋት ስሚጣልባቸው የገንዘብ መቀጫ ኃላፊነት አለበት፡፡

7) ስለሚሸጣቸው ዕቃዎች አጠቃቀም ለተጠቃሚው ወይም/እና ለሠራተኞቹ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያደርግ ሥልጠና መስጠት አለበት፡፡

8) አቅራቢው ዕውቅና የተጠየቀባቸውን መሳሪያዎች ስመፈተሽና ስመሞከር የሚያስፈልገውን ወጪ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡

9) አቅራቢው የመሳሪያዎች ብልሽት በተገለፀለት በ24 ሰዓት ውስጥ የጥገና አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

10) ከመሳሪያ አቅራቢው ጋር ውል የፈፀሙ የአገልግሎት ማዕከላት ሠራተኞቻቸው በመሳሪያው አምራች የሥልጠና ደረጃዎች መሠረት ሥልጠና እና የብቃት ማረጋገጫ ከአቅራቢው የተሰጣቸው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

11) የመሳሪያ አቅራቢዎች የተሰጣቸው ዕውቅና ወይም ስመሳሪያው የተሰጠ ዕውቅና ከተሰረዘ ይህንኑ ከሦስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ስተጠቃሚዎቻቸው የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

12) የመሳሪያ አቅራቢዎች የተዋዋሏቸው የመሳሪያ አገልግሎት ማዕከላት የሚያከናውኑትን ተግባር ካቆሙ ወይም ውላቸውን ካቋረጡ ይህንኑ በሦስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ስባስሥልጣኑና ስመሳሪያው ተጠቀሚዎች የማስታወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

13) ማናቸውም የመሳሪያው ተጠቃሚ ከአገልግሎት ማዕከል ጋር ያለውን ውል ካቋረጠ አቅራቢው በሦስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ስባለሥልጣኑ የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡

14) ተጠቃሚው የገዛውን መሳሪያ በጥቅም ላይ ማዋል እንዲችል አቅራቢው መሳሪያውን ሥራ ከማስጀመሩ በፊት ስባለሥልጣኑ ማሳወቅ ያለበት ሲሆን መሳሪያው ለየትኛው ማንንዣ ጥቅም ላይ እንደሚውልና ለዚህም አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ከተጠቃሚው የሚገኙትንም ጨምሮ በማቅረብ በባለሥልጣኑ ዘንድ ማስመዝገብ አለበት፡፡

15) አቅራቢው በየጊዜው በመሳሪያዎች ላይ የሚያደርጋቸውን አቅም የማሳደግ፣ ለውጥ የማድረግ፣ የማሻሻል ወይም ወቅታዊ አገልግሎት የማድረግ ሥራን ስባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 14. <u>ስለመሳሪያው ቴክኒካዊ ይዘት</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 2 ቁጥር 1 የተሰጠው ትርጓሜ እንደተጠበቀ ሆኖ መሳሪያ የሚይዛቸው ክፍሎች በአባሪ I እና II በዝርዝር መስፈርት የተዘጋጀላቸውና የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. በጭነቱ ላይ የሚታሰሩት የኤሌክትሮኒክስ ማሽጊያዎች (Electronic seals)፣

ለ. የኤሌክትሮኒክስ ማሽጊያዎቹን የሚያነበው መሳሪያ (AVL Reader)፣

ሐ. ተሽከርካሪው ያለበትን ቦታ የሚጠቁመው የGPS አካል፤

መ. መረጃውን ተቀብሎ ወደ ማዕከላዊ ሥርዓት በGPRS መስመር የሚልከው ሞደም፤

2) ማንኛውም ዕውቅና ያገኘ አቅራቢ የሚያቀርበው መሳሪያ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተመለከቱተን ክፍሎች ያካተተ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ከተመለከቱት ክፍሎች አንዳቸው ቢጎድሉ ወይም ቦርዱ የሚያወጣውን መሥፈርት ባያሟሉ መሳሪያው የተሟላ አይሆንም፤

3) አቅራቢው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተገለፀውን መሳሪያ ለፍተሻ ከማቅረቡ በፊት የቀረበው መሳሪያ ክፍሎች እርስ በእርስ የሚናበቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፤

4) አቅራቢው ሲያቀርብ ያሰበው መሳሪያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከሚጠቀምበት የGPRS ኔትወርክ እንዲሁም ከገዛቸው በኬላ ላይ ከተተከሉ የማንበቢያ አንቴና እና በእጅ ከሚያዙ ማንበቢያና መፃፊያ መሳሪያዎች ጋር በአግባቡ የሚናበብ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

5) የአቅራቢነት ዕውቅና ያገኘ ሰው መሳሪያዎችን ከማቅረቡ በፊት የሚያቀርበው መሳሪያ ባለሥልጣኑ ከዘረጋው ኔትወርክ ጋር ተጣጥሞ እንዲሰራ ማድረግ ያስችለው ዘንድ ዝርዝር የመናበቢያ ፕሮቶኮል (API) የሚያቀርበውን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ከባለሥልጣኑ ይሰጠዋል፤

6) አቅራቢው ሲያቀርብ ያሰበው መሳሪያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ካወጣው መሥፈርት በተጨማሪ ለስምሪት አገልግሎት ማዋል ያስችል ዘንድ በትራንስፓርት ሚኒስቴር የወጣውን መሥፈርት ማሟላት አለበት፤

## 15. <u>ስለመሳሪያ ዕውቅና እና ማመልከቻ</u>

1) ማንኛውም መሳሪያ ለሽያጭ ከመቅረቡ በፊት በቦርዱ ዕውቅና ማግኘት አለበት፡፡

2) የመሳሪያ አቅራቢ ለመሳሪያ ዕውቅና ለማግኘት የሚያቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ ሆኖ ስለመሳሪያው ባህሪያት የሚገልፀው መረጃም በአባሪ IV በተያያዘው ቅፅ ተሞልቶ መቅረብ አለበት፡፡ በዚሁ መሠረት፤

ሀ. በቅፁ ክፍል አንድ የመሳሪያው አምራች ስም፤ የአቅራቢው ስም፣ አድራሻ፤ የንግድ ስም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ይሞላል፡፡

ለ. በቅፁ ክፍል ሁለት የመሳሪያውን ስም፣ የምርቱን መለያ፣ ሞዴሉን የመሳሪያውን የተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች (ኤሌክትሮኒክ ማሽጊያዎች፣ ማንበቢያው፣ የጂ ፒ ኤስ መሳሪያና የጂ ፒ አር ኤስ ሞደም) መግለጫ ይሞላል፡፡

3) ባለሥልጣኑ የቀረበውን የዕውቅና ጥያቄ ለማስተናገድ ደረዳው ዘንድ በአንቀፅ 16 መሠረት የቀረበውን የመሳሪያውን ናሙና በራሱ አቅም ወይም ከተቋሙ ውጭ ካለ አካል ጋር ውል በመግባት ብቃቱን ያስመረምራል፡፡

4) የመሳሪያውን ብቃት የሚመረምረው የሥራ ክፍል ወይም የውጭ አካል በዚህ መመሪያ የተካተቱ መሥፈርቶችን እና የፍተሻ ቅደም ተከተል መግለጫዎችን በመከተል ተግባሩን ካከናወነ በኋላ ቦርዱ ባዘጋጀው ወጥ የሆነ የሪፓርት ቅፅ መሠረት ውጤቱን ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

5) ዕውቅና የተጠየቀለት መሳሪያ ተፈትሾ ያልተሟላ ሁኔታ ወይም ፍተሻውን የሚያዘገይ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር ውጤቱ አንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

## 16. ከመሳሪያ ዕውቅና መጠየቂያ ማመልከቻ ጋር ሲቀርቡ ስለሚገባ ማስረጃዎችና ናሙና

1) ማናቸውም ማመልከቻ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መረጃዎች መደገፍ አለበት፡፡

ሀ. የአቅራቢው የዕውቅና የምስክር ወረቀት እና የንግድ ፈቃድ የምሥክር ወረቀት ቅጂዎች፤

ለ. ዕውቅና የተጠየቀለት መሳሪያ ናሙና፤

ሐ. ዕውቅና የተጠየቀለት መሳሪያ የፕሮግራሙ መግለጫ እና የአወቃቀር ንድፍ ሰነዶች፤

መ. የመሳሪያው አጠቃቀም ማንዋል

2) ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት መረጃዎች ከዕውቅና መጠየቂያ ማመልከቻው ጋር ተያይዘው ካልቀረቡ ማመልከቻው እንደቀረበ ተደርጐ አይወሰድም፡፡

## 17. ስለአገልግሎት ማዕከል እና ሠራተኞች ግዴታ

1) አቅራቢው ወይም አገልግሎት መስጠቱ በውል የሚተሳሰፍለት ሰው ለሚያቀርባቸው መሳሪያዎች የጥገና እና የወቅታዊ ሰርቪስ አገልግሎት መስጠት የሚያስችለው በቦርዱ በሚገለፀው እና በአባሪ III በተለገፀው መሠረት የተሟላ ማዕከል ሊኖረው ይገባል፡፡

2) የጥገና ማዕከሉ መሳሪያ በሚጠግንበት ወይም በሚያድስበት ጊዜ ወይም ለሥራ በሚያዘጋጅበት እና በሚፈትሽበት ጊዜ ለመሳሪያው የተከናወነውን ሥራውን ያከናወነው ሠራተኛ የመሳሪያውን መለያዎች በመጥቀስ በመዝገብ ማስፈር ይኖርበታል፡፡

3) ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ የመሳሪያ ጥገና ወይም የሰርቪስ አገልግሎት በወቅቱ ማከናወን ይኖርበታል፡፡ ለዚሁ አገልግሎት የዋለውን ጊዜ በዝርዝር መመዝገብና ማሳወቅም ይኖርበታል፡፡

4) በፕገና ማዕከሉ ውስጥ ማንኛውንም ዓይነት ሌላ ተንዳኝ የሆነ አገልግሎትም ሆነ ሽያጭ ማከናወንና ከማዕከሉ ሠራተኞች ውጭ ሌሎች ሰዎች በማዕከሉ እንዲገኙ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል አራት

## የእውቅና ቦርድ አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት

### 18. *የቦርዱ አደረጃጀት*

1) የሚቋቋመው ቦርድ ቀጥሎ የተመለከቱት አካላት የሚወከሉ አባላት ይኖሩታል፡፡

ሀ. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተወካይ ሰብሳቢ፣

ለ. የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን ተወካይ፣

ሐ. የትራንስፓርት ሚ/ር ተወካይ፣

መ. የጭነት ደህንነት መከታተያና መመዝገቡያ መሳሪያ ቴክኒክ ባለሙያ ቡድን ተወካይ፣

ሠ. የመንገደ ትራንስፓርት ባሥልጣን ተወካይ፣

ረ.የጭነት ማመሳለሻ ባለንብረቶች ተወካይ፣

2) ቦርዱ ፀሐፊ ይኖረዋል፣

3) ቦርዱ ተጠሪነቱ ለባለሥልጣኑ ሲሆን በዋና ዳይሬክተሩ የሚመደብ የጽ/ቤት ኃላፊና አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

4) የቦርዱ አባላት ለሚያከናውኑት ተግባር እንደአስፈላጊነቱ በዋና ዳይሬክተሩ አበል ሲወሰንላቸው የሚችል ሲሆን የሥራ ቆይታ ጊዜያቸው ሁለት ዓመት ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ የሚራዘም ይሆናል፡፡

### *19. የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት*

1) በዚህ መመሪያ መሠረት፤

ሀ. ለአቅራቢነት ዕውቅና ለማግኘት፣

ለ. የመሳሪያ ዕውቅና ለማግኘት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን የመመረመርና፤

2) የመሳሪያ ዕውቅናና የአገልግሎት ሰጪነት ማዕከል ዕውቅና ለመስጠት በሚደረጉ የመሳሪያ ሙከራና የመስክ ጉብኝት የመገኘት፤

3) አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች የተሟሉ በሆነ ጊዜ ተገቢውን የውሳኔ ሀሳብ በአምስት የሥራ ቀናት ለዋና ዳይሬክተሩ የማቅረብ ኃላፊነት፤

5) ስለመሳሪያ ዕውቅና በባለሥልጣኑ ድረ ገፅና ሚዲያ የሚተላለፉ መረጃዎችን መመርመርና ማፅደቅ፤

6) የመሳሪያውን ብቃት ከሚፈትሹ አካላት ጋር ባለሥልጣኑ ውል እንዲገባና መሳሪያዎቹ እንዲፈተሹ የማድረግና በአጠቃላይ ቦርዱ ስላከናወናቸው ተግባራት በየስድስት ወሩ ሪፓርት ማቅረብ አለበት፡፡

7) ስለመሳሪያው ስለማደሻ ማፅከልና በመመሪያው ቦርዱ እንዲወስናቸው ወይም መስፈርት እንዲያወጣላቸው የተባሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 20. የቦርዱ አሰራር ሥርዓት

1) የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በየአስራ አምስት ቀኑ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ በቦርዱ ሰብሳቢ ተጨማሪ ስብሰባ ሲጠራ ይችላል፡፡
2) ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዐተ ጉባኤው የተሟላ ይሆናል፡፡
3) የውሳኔ ድምፅ አሰጣጥ በአብላጫ ድምፅ የሚወሰን ሲሆን እኩል ድምፅ በሆነ ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው የውሳኔ ሀሳብ ይሆናል፡፡
4) ቦርዱ የውስጥ አሰራሩን በውስጥ ደንብ ሊወስን ይችላል፡፡

## 21. የቦርዱ ፀሐፊ /የጽ/ቤት ኃላፊ/ ኃላፊነት

የጽሕፈት ቤት ኃላፊ የቦርዱ ፀሐፊና የሰብሳቢው ተጠሪ ሲሆን የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

ሀ) የቦርዱን ጽ/ቤት ይመራል፣ ያደራጃል፤

ለ) ለቦርዱ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን በሥርዓት መዝገቦ ይቀበላል፣ ይይዛል፣ ለውሳኔም ያቀርባል፡፡

ሐ) የቦርዱን የስብሰባ አጀንዳዎች ከሰብሳቢው ጋር ያዘጋጃል፣ያሳውቃል፣ ቃለጉባኤ ይይዛል፡፡

መ) ስለጽ/ቤቱ ሥራ ክንውን ሪፓርት በየሦስት ወሩ ለቦርዱ ሰብሳቢ ያቀርባል፡፡

ሠ) እንደአስፈላጊነቱ ከቦርዱና ከቦርዱ ሰበሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 26. የቁጥጥር ሥርዓቱ አፈፃፀም

መሳሪያዎችን በተሽከርካሪዎች ላይ ጥቅም ላይ ስለሚውሉበት ሁኔታ እና ስለቁጥጥር ተግባራት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚያወጣው የተለየ የአፈፃፀም መመሪያ ይገለፃል፡፡

### 27. ግዴታን መተላለፍ የሚያስከትለው ኃላፊነት

በዚህ መመሪያ የተጣሉትን ግዴታዎችና ክልከላዎች በመተላለፍ የሚፈፀሙ ጥፋቶች በአዋጁ እና በአዋጁ አንቀፅ 107/2/ በሚወጣ መመሪያ መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

### 28. ቅሬታ አቀራረብ

በዚህ መመሪያ መሠረት በባለሥልጣኑ አካላት የሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ የሚኖረው ማንኛውም ሰው በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 87 እና አንቀፅ 107 ንዑስ አንቀፅ/3 መሠረት ለባለሥልጣኑ የአቤቱታ አጣሪ ቡድን እንደዚሁም ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

### 29 መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ የሆናል፡፡

**አዲስ አበባ-------------------ቀን 2004 ዓ.ም**

**መላኩ ፈንታ**

**የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**